- 29 -

መንቃት ማለት ይህ ነው!

ስሜትን መግለጽ በጣም ከባድ ነው። ለምሳሌ ሕይወት ማለት ይኸው ነው ብለህ በማሰብ ሙሉ ዕድሜህን ዋሻ ውስጥ ኖርክ እንበል። ድንገት ለመጀመርያ ከዚያ ሕይወት ዘለህ ወጣህ። ሰማይን አየህ፤ ዛፎችን፣ ወፎችን እና ፀሐይን ተመለከትክ። በሕይወትህ ውስጥ ለመጀመርያ ጊዜ አንተ ታውቀው የነበረው ዓለም ውሸት መሆኑን ተገነዘብክ። ለመጀመርያ ጊዜ ውብ በሆነ መልኩ እውነትን አገኘህ። በዚህን ጊዜ እውነታውን መቀበል ምን ያህል ከባድ እንደሆነ አሰብ አስቲ። እንደወጣህ ለተወሰነ ጊዜ የትኛውንም ነገር መሥራት እንድምትችል ታስባለህ። ወዲያውኑ ደግሞ ዋሻው ውስጥ የነበረው ያለፈው ሕይወትህ ምንም እንዳልሆነ ትረዳለህ። ከዚያም ትልቅ ለመጀመርያ ጊዜ ኃይል ትልቅ መነቃቃት፣ ትልቅ ሕያውነት እና ትልቅ ንቃት ይሰማሃል። በርግጥም ያ ለመግለጽ ካባድ የሆነ ስሜት ነው። ይህ የመንፈስ ከፍታ የመጣው አዲስ ካገኘኸው እውነታ ጋር ተያይዞ ነው።

ይህ ነው መንቃት ማለት!።

ከሌላ እምነት አሊያም ሃይማኖት አልባ የሆነ ኑሮ በኋላ ወደ እስልምና የገባ ሰው ይህንን ስሜት ያውቀዋል። ሙስሊም ሆኖ የተወለደና ወደ ዲኑ እንደገና የመጣ ሰውም ይህንን ስሜት ያውቀዋል። የትኛውም ከአላህ ርቆ ይኖር የነበረና ወደ አላህ የተመለሰ ሰው ይህንን ስሜት ያውቀዋል።

ኢብኑ አል-ቀይም (አላህ ይዘንላቸው) "መዳሪጅ አስ-ሳሊኪን" በተሠኘው መጽሐፋቸው ይህንን ስሜት "የቅዟህ/ መንቃት" ይሉታል። ድንገት ከእንቅልፍ እንደመንቃት፣ ብንን ብሎ አንድን ነገር ማወቅ ሊሆን ይችላል። አሊያም ደግሞ የልብ ሁሉን ነገር ድንገት ማወቅ፣ "የልብ ሕያውነት" የምንለው ሊሆን ይችላል። ይህንኑ ሁኔታ "ወደ አላህ መንገድ የሚደረገው ጉዞ የመጀመርያው ክፍል ነው።" ይሉታል - ኢብኑል ቀይም።

ይህ ሁኔታ አንዳንዴ "የመቀየር ጉጉት" የሚባለው ነው። አንድ ሰው ለመጀመርያ ጊዜ ወደ አላህ መንገድ ሲቀየር ወይም ደግሞ መምጣት ሲጀምር አብዛኛውን ጊዜ ሌሎች የሌላቸውን ትልቅ መነሳሳት እና ጉልበት ይኖረዋል። የዚህ ጉልበት ምንጩ ይህ እርከን በባህሪው መንፈሳዊ ደረጃው ከፍ ያለ በመሆኑ ነው።

CamScanner

CamScanner

የዚህ እርከን የመንቃት ባህሪዎች

የአምልኮ ተግባራትን (ዒባዳዎች) መግራት -

በዚህ እርከን ላይ ዒባዳ (አምልኮ) መፈፀሙ በጣም ቀላል ይሆናል። ሰውዬው ጉጉ እና እጅግ የተነሳሳ በመሆኑ አዲስ ለደረሰበት እውነታ የትኛውንም መስዋእት ለመክፈል ዝግጁ ይሆናል። ይህ ከፍተኛ የመነሳሳት ሁኔታና ጉጉት በአንድ ጊዜ ሰውየውን ከዜሮ ወደ ስልሳ ደረጃ እርከን ያመጥቀዋል። ትልቅ መንፈሳዊ ንጥረ ነገሮችናን ግብኣቶችን እንደ መሞላት ነው። በዚህ ሁኔታ ላይ ያገኘኸው ጥንካሬ ምንጩ ካንተ ከራስህ አይደለም። ባንተ ውስጥ እንዲቀመጥ የተደረገና የተሠጠህ የቅናቻ ችሮታ ነው። አንዳንድ ሰዎች በአንድ ጊዜና በፍጥነት በትልቅ ሁኔታ መቀየር እንደሌለብህ ሊመክሩህ ይችላሉ። በበኩሌ በፍጥነት መለወጡ ችግር መስሎ አይታየኝም። ግና መሃይምነት ነው ትልቁ ፍጥነት። ተስፋ መቁረጥ ነው ትልቁ ፍጥነት። አላህ አንተ መጠቀም በምትችልበት ሁኔታ አንድን ስጦታ የሠጠህ እንደሆነ ተጠቀምበት። ግና ስጦታውን አመስግነው። የዚህ ችሎታ ምንጩ አንተ አይደለህምና። የከፍታ ሁኔታ ደግሞ ብዙ እንደማይቆይ ማወቅ ያስፈልጋል። በአጭር ጊዜ ከዜሮ ወደ ስልሳ መሸጋገር የምትችል ከሆነ አድርገው። ግና የከፍታ ጊዜው ካለፈ በኋላ ተስፋ በመቁረጥና በመንሸራተት ወደ ዜሮ መመለስ የለብህም።

ጊዜያዊነት -

ሌላው የዚህ እርከን የመንቃት ባህሪ ንቃቱ ጊዜያዊ መሆኑ ነው። በዚህ ምድራዊ ሕይወት ላይ እንደሚያጋጥመው እንደማንኛውም እርከን ሁሉ ይህ እርከንም ጊዜያዊ ነው። ሕይወት ቀጥ ያለች መስመር አይደለችም። አባጣና ጎርባጣ አላት። ቁልቁለትና ዳገትን ይዛለች። ወደ አላህ የሚደርሱበት መንገድም እንዲሁ ቀጥ ያለ አይደለም። ብዙ ውጣውረዶች ያሉበት ነው። ግና ይህን በትክክል አለመረዳት ተስፋ ወደ መቁረጥ ያደርሳል።

በዚህ እርከን ላይ የሚያጋጥሙ አደገኛ ወጥመዶች

እነኚህ ወጥመዶች ወደ አላህ መንገድ ላለመንቀሳቀስ ሁለቱ ምክንያቶች ናቸው - አጉል ጉራ እና ተስፋ መቁረጥ። ጉራና ኩራት ያለበት ሰው ሙሉ በሙሉ የተሟላሁ ነኝ፤ ምንም አያስፈልገኝም ብሎ ስለሚያስብ አይሠራም፣ አይማርም፤ ለተጨማሪ ዕድገት ጥረት አያደርግም፣ አይታገልም። ተስፋ የሚቆርጥ ሰው ደግሞ ጥሩ ሰው አይደለሁም ብሎ ስለሚያስብና ሁልጊዜም የጥፋተኝነት ስሜት ውስጡን ስለሚቦረቡረው ጥረት ከማድረግ ይሳነፋል። በዚህ እርከን ላይ ሁለት ተቃራኒ ስሜቶች ያሉ ሲሆን ወደ አንድ

CamScanner

CamScanner

ተመሳሳይ ውጤት ማለትም ወደ አላህ መንገድ ከመጓዝ የሚያግዱ ናቸው። ስለዚህም እነርሱን መጠንቀቅ ይገባል።

አጉል ጉራ እና ከመጠን በላይ መወጣጠር-

የመጀመርያው ወጥመድ በአምልኮ ተግባራት ላይ መበርታትና መጨመር ከአላህ እገዛ የሚመጣ መሆኑን አለመገንዘብ ነው። ለመልካም ሲባዳ መታደል የግል ጥረት ውጤት አይደለም። ይህንን በትክክል ያልተረዳ ሰው በኢማን አምልኮ ከፍታ ላይ የደረሰው በራሱ ልፋት እንደሆነ ያስባል። የዚህ ዓይነቱ አረዳድ እጅግ አደገኛ ስህተት የተሞላበት ነው። ምክንያቱም ወደ መታበይና በራስ መመፃደቅን ያስከትላልና ነው። በዲን ከፍ የማለቱ ሁኔታ ከአላህ ችሮታ መሆኑን መርሳት አይገባም። አላህ (ሱ.ወ.) ነው የሚያድለው። በዚህ ጥመድ የተያዘና በጥሩ ሁኔታ በአምልኮ ተግባር ላይ የተሠማራ ሰው የመመጻደቅና የመደነቅ ስሜት ውስጡ ይፈጠራል። ሌሎችንም መናቅ ይጀምራል።

ተስፋ መቁረጥና እጅ መስጠት-

ይህ ስሜት የሚመጣው በሕይወታችን ውስጥ እንደማንኛውም ነገር ሁሉ በመንፈስ ከፍ ማለት ጊዜያዊ መሆኑን ካለመረዳት ስህተት ነው። ወረድክ ማለት ወድቀሃል አሊያም ደግሞ ስህተት ነገር ፈፅመሃል ማለት አይደለም። በዚህ ዙርያ ብዙዎቻችን ከረመዷን መውጣት በኋላ ስንወርድ ምንም ዓይነት ስሜት እንደሚሰማን እናስታውስ።

ከፍ እንዳሉ መቆየት የዚህ ዓለም ባህሪ አይደለም። አይደለም እኛ ሌላው ቀርቶ ታላቁ ሶሐባ ከአቡበክር (ረ.ዐ.) ሕይወት ጭምር ይህንኑ እንረዳለን። አንድ ቀን አቡበክር እና ሐንዞላ (ረ.ዐ.) ወደ አላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ዘንድ መጡ። ሐንዞላ "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ ሐንዞላ ንፍቅና ገብቶታል።" አለ። አላህ መልዕክተኛም (ሰ.ዐ.ወ.) "ምንድነው አሱ?" አሉት። ሐንዞላም "እርሶ ጋ ስንሆንና እርሶ ጀነትና እሳትን ሲያስታውሱን ልክ በዐይናችን እንደምናያቸው ሆነን አላህ እንፈራለን። ከርስዎ ስንለይ ደግሞ ሚስቶች እና ልጆች ይቀራመቱናል፤ በዚህም በአሳፋሪ ሁኔታ ውስጥ እንሆናለን።" አለ። የአላህ መልዕክተኛም (ሰ.ዐ.ወ.) "ነፍሴ በእጁ በሆነችው እምላለሁ፤ አላህን ከማውሳት አንጻር እኔ ዘንድ በነበራችሁበት ሁኔታ ብትቆዩ ኖሮ መላእክት በአልጋዎቻችሁና በጎዳና ላይም ጭምር በጨበጧችሁ ነበር። ነገር ግን ሐንዞላ ሆይ አንዴ እንዲህ አንዴ እንዲያ ነው (ከፍ ዝቅ ያለ ነው፤ የሰው ልጅ በተመሳሳይ ሁኔታ አይኖርም።)" አሉት። (ሙስሊም እንደዘገቡት)

CamScanner

CamScanner

የኢማን ከፍታ ካለፈ በኋላ

የዚህ ጉዞ እጅግ ወሣኙ ከፍል ፈጽሞ ተስፋ አለመቁረጥ ነው። ሁሌም አንድ ዓይነት ከፍታ ላይ መቆየት እንደማይኖር ልናውቅ ይገባል። ይህ ነገር የሆነው እኛ ስላጠፋን አይደለም። እንደማንኛውም መንገድ ሁሉ ከከፍታ በኋላ ዝቅታና ቁልቁለት ይመጣል። የአላህ መልዕከተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ለአቡበከር (ረ.ዐ.) የገለፁትም ይህንኑ ነው። ከፍ እና ዝቅ ማለት፤ መውጣት እና መውረድ በሕይወት ውስጥ ያለ ነገር ነው። የማይቀር የሕይወት ክፍል ነው። ሁሌ ከፍታ ላይ እንደሆንን ብንዘልቅ ኖሮ የሰው ልጅ ባልሆንን ነበር። መላኢካ በሆንን ነበር። የስኬት ቁልፉ በከፍታ ላይ በነበርን ጊዜ የምንሠራው ሥራ አይደለም። ዝቅታ ላይ በነበርን ጊዜ የከፍታ ስሜት ሳይሰማን የምንሠራው ነው። በዚህ መንገድ ላይ ስኬት ለማግኘት ትልቁ ቁልፍ አንድ ጊዜ ዝቅታ ላይ ከደረስን በኋላ ዝቅታ የሚያጋጥም መሆኑን አውቀን ወደ ከፍታ ለመመለስ መፍጨርጨር ነው።

የሸይጧን መረቦች

ሸይጧን የተለያዩ ሁኔታችንንና ደካማ ጎናችንን በማጤንና በመገምገም በተለያዩ መንገዶች ወደኛ እንደሚገባና በቁጥጥሩ ሥር እንደሚያውለን ማወቅ ይኖርብናል፡-

ከፍታ ላይ ስንሆን - ከፍታ ላይ ስንሆን፤ እንድንታበይ በማድረግ ሊጠልፈን ይሞክራል። በመታበያችን እሱ ይጠቀማል። ሌሎችን ዝቅ አድርገን እንድንመለከት ያደርገናል። በራሣችን የኢማን ሁኔታ እንድንደሰት፣ ከማንም በላይ እንደሆንን እንድናስብ፣ ከፍታ ላይ የደረስን በመሆኑ ከዚህ በላይ ለመጣር ማሰብና መነሳሳት እንደሌለብን ሹክ በማለት ያጃጅለናል። በዙርያችን ካሉት ከሁሉም እንደምንበልጥ ያስመስልብናል። ሁሌም የሚያሳየን ከኛ በታች ናቸው ብለን ያሰብናቸውን ሰዎች ነው። በዚህም ከፍተታችንን እንዳናይ ያደርገናል። ለምሳሌ ፡- ሒጃብ የማትለብሺ ከሆነ ሒጃብ ለብሰው እንዲህ እንዲያ ያሉ መጥፎ ወንጀሎችንና ሥራዎችን የሚሠሩ አሉ እንድትይና የሌሎችን ጥፋት በመከታተል ተወጥረሽ ወደ ራስሽ እንዳትመለከቺ ያደርግሻል። ከነርሱ መጥፎ ሁኔታ የኔ ሒጃብ አለመልበስ ይሻላል፤ እንድትይና በዚሁ ባለመልበስ የተሳሳተ ሁኔታሽ እንድትገፊ ያደርግሻል። ወይም ደግሞ በሶላት ጉዳይ ችላ የምትል ዓይነት ሰው ከሆንክ ቢያንስ ከዚህ የባሰ ወንጀል እየሠራሁ አይደለሁም። አልጠጣም፣ ወንጀል፣ አልሠራም .. እንድትል ያደርግሃል። አላህ በከፍተኛ ጥመት ሰዎችን የሚመነዳ አይደለም። የሌሎች ሥራ እኛን አይመለከተንም። ሁሉም በየሥራው ነው የሚመዘነው። የትንሳኤ ቀን ሁላችንም ብቻችንን ነው አላህ (ሱ.ወ.) ፊት የምንቆመው። ይህ እንግዲህ ጥረት እንዳናደርግ ሸይጣን እኛን ለመግታት የሚጠቀመው መሣሪያ ነው።

CamScanner

CamScanner

ዝቅታ ቦታ ላይ- ዝቅታ ቦታ ላይ ስትሆን ሸይጣን በተለየ መንገድ ነው የሚመጣብህ። ሸይጣን ተስፋ በማስቆረጥ ነው አንተን ለማቆም የሚያጠምድህ። ምንም ጥቅም እንደሌለህ፣ ካሁን በኋላ ማገገም እንደማትችል፣ መፍጨርጨርም፣ መሞከርም መጣርም እንደሌለብህ ሊያሳምንህ ይሞክራል። ምንም ነገር ብትሠራ፣ ልፋት ካልሆነ በስተቀር መውደቅህ ቅርብህ መሆኑን ይነግርሃል። በዚህም የተነሳ በፊት ወደነበርክበት ሁኔታ መመለስ ይከብድሃል። ወይም ደግሞ አንተ ምህረት የማይገባህ እጅግ መጥፎ ሰው እንደሆንክ አድርጎ ይነግርሃል። በዚህም የተነሳ ሳትወድቅ ትወድቃለህ፣ የባሰውኑ ከአላህ መስመር ትወጣለህ፣ የአላህን መንገድ ትሸሻለህ። ምናልባት አንድ የሆነ ጊዜ ተነስተህና ተመልሰህ ብዙም ሳትቆይ በመንሸራተትህ ምንም እንደማትረባ እና ተስፋ እንደሌለህ አድርጎ መስረጃ ይቆጥርብሃል። ከዚህ ቀደም ጥሩ ሁኔታ ላይ በነበርክበት ጊዜ ጠንካራ ስለነበርክ ሰዎች ሲሳሳቱ ወይም ሲደክሙ የማትቀበል የነበርክ መሆንህን ያስታውስሃል። ይህ ድሮ በሰዎች ላይ የነበረህ አመለካከትህ መልሶ አንተኑ ይጎዳሃል። ለስህተትህና ለድክመትህ ምክንያት እና ይቅርታ ትነፍገዋለህ።

ሰው መሆንህንና ደካማ መሆንህን ረስተህ ስህተት በፈጸምክ ጊዜ ለራስህ ምክንያት መስጠት እንደማይገባህ ካመንክ በገዛ ራስህ ላይ ጨካኝ ትሆናለህ፤ ከራስህም ተስፋ ትቆርጣለህ። እንዲህ መሆን አልነበረብኝም፤ ካሁን በኋላ ተስፋ የለኝም፤ ከወደቅኩበት አልነሳም ትላለህ። ራስህን ትጥላለህ። ራስህን ትጠላለህ። እንደውም ተጨማሪ ኃጢአቶችን ሁሉ ልትሠራ ትችላለህ። ይህን ማድረግህ ደግሞ በወንጀል ላይ ወንጀል ጨምሮ የባሰውኑ ተስፋ ያስቆርጥሃል እንጂ ምንም አይጠቅምህም። ከገባህበት የጭቃ እሾህ እንዳትወጣ ያደርግሃል። ሸይጣንም በስህተት ላይ ስህተት እንድትደራርብ እየተመላለሰ ሹከ ይልሃል። ተውባ እንዳታደርግና ወደ አላህ እንዳትመለስ፤ እንዲሁም ያንተ ዓይነት ሰው የለየለት ሙናፊቅ ነውና ሶላት መስገዱ፣ መፆም መፀለይህ ጥቅም የለውም በማለት ከብዙ የአምልኮ ተግባራት ያስንፍሃል። ከአላህ እዝነት ተስፋ እንድትቆርጥ ያድርግሃል። እሱ የሚፈልገውም ይህንኑ ነው። እነኚህ ሁሉ ውሸቶች መሆናቸውን ልታውቅ ይገባል። ግና እሱ በሚሠራው ነገር የተካነ ነውና እስከትወድቅ ይከተልሃል። አንተን ለማሳመን የቻለውን ርቀት ሁሉ ይሄዳል። እንደውም ከሌላው ጊዜ በበለጠ ወደ አላህ መመለስ ያለብህ ኃጢአት ላይ በወደቅክ ጊዜ መሆን አለበት።

እንዲህ ወደኋላ ከመንሸራተት ሁኔታ ራስህን መጠበቅ የፈለግክ እንደሆነ፤ የመንሸራተት እና ዝቅታ ቦታዎች የመንገዱ አካል እንደሆኑ መርሳት የለብህም።መውደቅም ሆነ መነሳት የሰው ልጅ የሕይወቱ አካል ነው። ይህንን ካወቅክ በወረድክ ጊዜ ውድቀት አይሰማህም። ተስፋ መቁረጥ አያገኝህም። ሙናፊቅም አይደለህም። ይህንኑ ስሜት ነበር እነ አቡበከር ለአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) የተናገሩት። እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ከደረሰብህ ተስፋ ከመቁረጥ ራስህን ጠብቅ። ዋናውና ቁልፉ ነገር ሙሉ በሙሉ እንዳትወድቅ የሚያደርጉህ

CamScanner

CamScanner

አንዳንድ ባህሪዎችን ማዳበር ነው። የቱን ያህል ቢሰማህም፣ የቱን ያህል ሞራልህ ቢወድቅም፣ የቱን ያህል ብትወርድም፣ ነገሮችን አሁንም የቻልከውን ያህል መሥራት ይኖርብሃል። በወረድክ ጊዜ በርግጥ ተመልሶ መነሳቱና ማገገሙ ሊከብድ ይችላል። ግና መታገልና ማገገም ግድ ነው። ለምሳሌ - በትንሹ ምትሠራው ከሆነ በቀን ውስጥ አምስት የግዴታ ሶላት ነው እንበል። የቱን ያህል ብትወርድና መጥፎ ስሜት ቢሰማህም እነኚህን ነገሮች ፈጽሞ መተው የለብህም። በግዴታ ሶላቶችህ ልትደራደር አይገባም። ሶላቶችህን እንደምትሰበው አየር ነው ማየት ያለብህ። ያለ አየር መኖር አይቻልም። በደከመህ እና ጥሩ ስሜት ላይ ባልሆንክ ቁጥር መተንፈስ የለብኝም ብለህ ካሰብክ/ከወሰንክ ሊከሠት የሚችለውን ነገር አስተውል።

በትንሹ መወጣት ካለብህ ልምድ መካከል ሌላም መጥቀስ ይቻላል። ለምሳሌ በቀን ውስጥ የተወሰኑ ትርፍ ሶላቶችን እና አዝካሮችን ትፈጽም ይሆናል። ወይም ደግሞ ከቁርአን ትንሽም ብትሆነ የተወሰነ ክፍል ታነብ ይሆናል። አላህ ብዙ እየሠሩ ከማይጸኑበት ሥራ በላይ ትንሽ ቢሆኑም በተከታታይ የሚሠሩ ሥራዎችን እንደሚወድ ማስታወስ ይኖርብሃል። በወረድክበት ጊዜ የተወሰኑ መሠረታዊ ነገሮችን ይዘህ የምትጓዝ ከሆነ፤ በሆነ ጊዜ የኢማንን ማዕበል ትሳፈርና ወደነበርክበት ትመለስ ይሆናል ኢንሻአላህ። አላህ ብሎ የተመለስክ ጊዜ በፊት ከነበርክበት የከፍታ ሁኔታ በላይም ዳግም ከፍ ትል ይሆናል።

የሰው ልጅ በአላህ መንገድ ላይ የሚያደርገው ጉዞ ቀጥ ያለና ለጥ ያለ አለመሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል። ኢማን ከፍ እና ዝቅታ አለው። የማምለክ ሁኔታችንና አቅምም ከፍ እና ዝቅ ይላል። ነገር ግን ማወቅ ያለብን ነገር ቢኖር ለዝቅታ ነገር ሁሉ ከፍታ ያለ መሆኑን ነው። ስለሆነም መታገስ ያስፈልጋል። መጽናት ግድ ይላል። ተስፋ አለመቁረጥ ይገባል። ሁሌም የአላህን እርዳት መሻት ነው የሚያዋጣው። መንገዱ ቀላል አይደለም ከባድ ነው። መውደቅና መነሳት አለው። ነገር ግን በሕይወታችን ውስጥ እንደሚያጋጥመን ማንኛውም ሕይወት ሁሉ ይህ መንገድም ፍጻሜ አለው። የሚያልቅና ፍፃሜ ያለው መሆኑም ተገቢ ነው።

አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلۡإِنسَٰنُ إِنَّكَ كَادِحٌ إِلَىٰ رَبِّكَ كَدۡحٗا فَمُلَٰقِيهِ ﴾

«አንተ ሰው ሆይ! አንተ ጌታህን (በሞት) እስከምትገናኝ ድረስ ልፋትን ስፈ ነህ፤ ተገናኚውም ነህ።» (አል- ኢንሺቃቅ : 6)

CamScanner

CamScanner